የምስጋና መዝሙራት

1, ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር /2/ ምስጋና ይገባሃል /2/

ለዚች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም በጤና

አደረስከን/2/

2. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለው

ላመሰግነው እንጂ/2/ሌላ ምን እላለሁ

3.እግዚአብሔር ይመስገን

እግዚአብሔር ይመስገን ይህችን ቀን ቀድሶ ለሰጠን እኛ (2)

ከያለንበት ሰብስቦ (2) ለዚህ ያደረሰን (2)

4. ቸርነቱ

ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ (2)

ይክበር ይመስገን መድኃኒዓለም የዓለም ቤዛ(2)

5. አስተምሮናልና

አስተምሮናልና መክሮናልና ገስፆናልና(2)

እግዚአብሔር ይድረሰው ምስጋና(2)

6.ንሴብሖ

ንሴብሖ /2/ ለእግዚአብሔር /2/

ስቡሐ ዘተሰብሐ /4 /

እናመሰግነው /2/ እግዚአብሔርን /2/

ምስጉን ነው የተመሰገነ /4/

አዝ

ባህሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ

በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ

ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን

ህያወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን

አዝ

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል መከራም ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

አዝ

ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ እንደጠጣነው

ይህን ታላቅ አምላክ ኑ እናመስግነው

ሰዎች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል

ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

አዝ

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል ፈተናው ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

7. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን/2×/
አምላክ አለ መሃላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን እድሜ ለጨመረልን
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን
ኃጢአትህን ይታገስሀል
በምሕረት አምላክ ያይሀል
ደስታ ነው በሰማያት
የአንድ ኃጥእ የጽድቅ ህይወት
አልል በሉ የጎበኛችሁ
በምሕረት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ላሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትጸልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አምላክ ያስበን

8. ለዚህ ላደረሰን

ለዚህ ላደረሰን በሰላም በጤና/2×/
<u>ሃሌ ሃሌ ሉያ</u>(2×) እናቅርብ ምስጋና/2×/
ስራችንን አይቶ በደላችንን
ኃጢያታችን አይቶ ሰውነታችን
ያን ሁሉ ታግሶ ለዚህ ላበቃን
<u>ሃሌ ሃሌ ሉያ</u>(2×) እናቅርብ ምስጋና/2×/
አንተ በምሕረትህ በፀቅርታ ጎብኘን
የአንድ ቀንም እድሜ ስለጨመርክልን

ቸሩ አምላካችን ሆይ አንተን እናመሰግን
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2×) እናቅርብ ምስጋና/2×/
ጌታ አምላካችን ሆይ ተስፋችን አንተ ነህ
እምነታችን ያጽና ፈቃድህ ይሁንልን
አንተ በምሕረትህ በያቅርታ ጎብኘን
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2×) እናቅርብ ምስጋና/2×/

9. አድርገህልኛልና
አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሃለሁ እልል(2×)
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም
ቀኑ ጨልሞብኝ ዙርያው ጉደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄያለሁ
ካለኝ ነገር ሁሉ በአንተ ታምኛለሁ
ጥቂቷን አብዝተህ የምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ስጦታ
በቀንም በሌሊታ ሁሌ የሚያበራ
መንክር ለባህሪህ እጹብ የአንተ ስራ
አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ደህ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

10. አማን በአማን
አማን በአማን/2×/
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ/2×/
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በደል ብትቆጥር ጌታ
የእኔስ ኃጢአት የለውም ቦታ
በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
የእኔስ ኃጢአት ቢበዛ ምንም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
ምሕረትን ልከህ አድነን ዛሬ
ታውቀኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበቺኝ
በጽድቅ በደስታ መኖር አቃተኝ
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

11. እንደ እግዚአብሔር ያለ
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና/2×/
እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና/2×/
ባህር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ
ፈርዖን ወደቀ አልሰራም ትምክህቱ
ደካሞቹ ጸንተው ተራመዱ
ኃይለኞቹ ይኸው ተዋረዱ

የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው
ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው
ኃይለኞቹ ቢበረታቱብን
እንጸናለን በእርሱ ተደግፈን

የተወረወረው የጠላታችን ጦር
ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር
የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው
ከሀሊ ነው የለም የሚሳነው

12.ኑ በእግዚአብሔር
ኑ በእግዚአብሔር <u>ደስ ይበለን</u>(2×)/2×/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን/2×/

የሰማዩን መንግስት ርስቱን ለሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን
ለዚህ ድንቅ ውለታ ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል

ከዐለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስግነው ከጠዋት እስከ ማታ

በቃያስ በረሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛበት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተሰኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት

በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሐና የኢያቄም የአምነታቸው ፍሬ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስእለቱ የሐና እምነት
ለምኜልን ለእኛ ኪዳነ ምሕረት

13. ቸርነትህ ነው
ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከ ዛሬ
ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከ ዛሬ
ላመሰግንህ የእኔ ጌታ በዝማሬ/2×/

መከሊቴን ቀብሬ ባሳገዝህ
መብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ
በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ
በፍቅርህ ጎብኝተህ ከሞት አውጣኝ
ከቤትህ ርቄ መኝ ጠገብኩኝ
በረሀብ እርዛት ተቸገርኩኝ
አምናለሁ አምላኬ እንድትምረን
ለይቅርታ መጣሁ ተቀበለኝ

አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ
በአንተ ቸርነት ግን እመካለሁ
የከበደ ሸክሜ ይቀለኛል
ይቅርታ ለባሪያህ ይደርሰኛል
ከመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር
ስራህን ለትውልድ ለመመስከር

እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ
አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ
በሰው እጅ መመካት አቁሜያለሁ
ረዳቴ አንተ ነህ አውቄያለሁ
አንተ ከጠበቅከኝ በህይወቴ
ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ
የእኔን ስራ ተወው ምግባሬን
የመስቀሉን ነገር መርሳቴን
አዚሜን አንስተህ አንተን ልይህ
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

14.ሰላም ሰላም ለኪ

ሰላም(2) ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ(2)

አ.ዝ

የሕይወት መሠረት..... ሰላም ለኪ

የፍጥረት አለኝታ .....ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

ሁኝልን መከታ..... ሰላም ለኪ

አ.ዝ

በላዔ ሰብ ዳነ .....ሰላም ለኪ

ብዙ ነፍስ አጥፍቶ .....ሰላም ለኪ

ያንቺን ስም ለጠራ .....ሰላም ለኪ

ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ .....ሰላም ለኪ

አዝ

ተማጽነንብሻል .....ሰላም ለኪ

ባማላጅነትሽ..... ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

አማልጅን ከልጅሽ..... ሰላም ለኪ

አ.ዝ

እኛም ብንከተል .....ሰላም ለኪ

በጎ ምግባርን .....ሰላም ለኪ

በሰላም በጤና .....ሰላም ለኪ

እንኖራለን .....ሰላም ለኪ

15. ትምክተ ዘመድን

ትምክተ ዘመድን (2)ማርያም እምነ

ማርያም ትምክቱ ዘመድን

አዝ

የድንታችን አርማ የነፃነታችን

የህይወት መሠረት ነሽ ድንግል እናታችን

አንቺ ለኛ ዘርን ባያስቀር እንደ ጥንቱ እንደ ሰዶ ምድር

ሁላችን በጠፋን ነበር

አዝ

የአብርሀም ድንኳን ነሽ አምላክ ያደረብሽ

የጌዲዮን ፀምር ለይቶ ያከበረሽ

የኛ ቤዛ በጉ የተያዘብሽ

የዋህ ርግብ ከአበው ስር የተገኘሽ

እፀሳቤት የህይወት ሀረግ ነሽ

አዝ

አምላክ ከሰማይ ሆኖ ይቺን አለም ሲቃኝ

ንፅዩት ቅድስት ሆነሽ ማርያም አንቺን ቢያገኝ

ትህትናሽን ህይወትሽን ወዶ

ቃል ሰው ሆነ ከሰማያት ወርዶ

አከበረሽ በፍፁም ተዋህዶ

አዝ

የመዳናችን ምክንያት የሰው ልጆች ሰላም

ከሀጢያት ከመርገም የዳነብሽ አለም

አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን

በሲኦል ውስጥ ተግዘን የኖርን

ድንግል ባንቺ ነፃነት አገኘን

16.ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ

ይእቲ ክብረ ቅዱሳን/2/

ሙዳየ መና ግሩም/6/

የቅዱሳኑ ክብር ነሽና

እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና

የወለድሽልን የሕይወት መና

ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ

ፅንስ ያዘልላል ሰላምታ ድምጽሽ

እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል

ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል

የፀሃይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ

ታላቁን ብርሃን አየንብሽ

አትጨልምም ሕይወታችን

ልጅሽ ስላለ ፀሐያችን

ሰአሊለነ ሰላም ለኪ

ተማህፀነ በኪዳንኪ

ንዒ እርግብየ ምስለ ወልድኪ

ሰማይ ወምድር ያወድስኪ

17. ለማርያም

ለማርያም/2/

እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/

አ.ዝ

የተዘጋች ደጅ ለዘለዓለም

ህዝቅኤል ብሏል ለዘለዓለም

ንፅሕት ናት በእውነት ለዘለዓለም

በፍጹም ድንግል ለዘለዓለም

አብነት አድርገን ለዘለዓለም

አኛም እርሱን ለዘለዓለም

በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን**(2)**

አ.ዝ

የዋህነት ርግብ ለዘለዓለም

ሰላም አብሳሪ ለዘለዓለም

ለጨለማ ሕይወቴ ለዘለዓለም

ብርሃንን አብሪ ለዘለዓለም

እማጸንሻለሁ ለዘለዓለም

ድንግል ለነፍሴ ለዘለዓለም

አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ**(2)**

አ.ዝ

እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም

ያለኝ ፍቅር ለዘለዓለም

አይወሰንም ለዘለዓለም

አይነገርም ለዘለዓለም

በእርሷ ደስ ይለኛል ለዘለዓለም

ሐሴት አደርጋለሁ ለዘለዓለም

ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ**(2)**

አ.ዝ

ነይ ነይ ስላት ለዘለዓለም

ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም

አትለየኝም ለዘለዓለም

ለእኔስ ቅርቤናት ለዘለዓለም

አፁብ አፁብ ብለው ለዘለዓለም

አመሰገኗት ለዘለዓለም

ክብሯን ሊገልፁት ቢያጥራቸው ቃላት

18.ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም(2)

እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም (2)

አዝ

ንጽህት ስለሆንሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

እንከን የሌለብሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

የፍጥረታት ጌታ .....እመቤቴ እመቤቴ

ባንቺ አደረብሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

የድንግል መመረጥ.....እመቤቴ እመቤቴ

ዜናው አስገረመኝ .....እመቤቴ እመቤቴ

እሳቱን ታቀፍች .....እመቤቴ እመቤቴ

የማይቻለውን .....እመቤቴ እመቤቴ

ትህትናሽ ግሩም ደግነትሽም እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም
አዝ

ምርኩዜ ልበልሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

ጥላ ከለላዬ .....እመቤቴ እመቤቴ

ጋሻዬ ነሽ አንቺ .....እመቤቴ እመቤቴ

ለኔስ መመኪያዬ .....እመቤቴ እመቤቴ

ባለም እንዳልጠፋ.....እመቤቴ እመቤቴ

ህይወቴ መሮብኝ.....እመቤቴ እመቤቴ

እንደወይን አጣፍጪው ....እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል ድረሺልኝ .....እመቤቴ እመቤቴ

ትህትናሽ ግሩም ደግነትሽም እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም

አዝ

የምስራቅ ደጃፍ ነሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

የሁላችን ተስፋ .....እመቤቴ እመቤቴ

እሙ ለፀሐይ ጽድቅ.....እመቤቴ እመቤቴ

የሁሉ ጠበቃ.....እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል የድል አክሊል.....እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል የጽድቅ ስራ..... እመቤቴ እመቤቴ

ድንግል መሰላል ነሽ .....እመቤቴ እመቤቴ

የተዋህዶ ተስፋ.....እመቤቴ እመቤቴ

ትህትናሽ ግሩም ደግነትሽም እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም

19. እመቤቴ የአምላክ እናት
እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘወትር ነፍሴ(2)

ልቤ ተነሳሳ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍጹም ትህትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን

የታጠረች ተክል እመ ብዙኃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባታል ዘወትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቶት
ያንን የእሳት ባህር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

20. ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና
አዝ
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙን መድኃን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአሕዛብ ሀገር ስኖር ተሸጨ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
አዝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ
አስተናባሪው በቄንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለው ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት አሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመአምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
አዝ
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህቺ ዓለም ንቃ ገፍታ ብተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
ዐውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያሰቃየኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
አዝ
ከፋዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ
አንቺን መውደዴን አያስተውኝ
በአሕዛብ መሐል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

21. ያዕቆብ ከቤርሳቤህ
ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን ሲሄድ
የለውም ነበረ አማካሪ ዘመድ
ፀሐይ ጠልቃ ነበር ከዚያ እንደደረሰ

ከአራቱም በታች ድንጋይ ተንተራሰ
ህልምንም አለመ ታላቁን ራዕይ
መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ
ሲወጡ ሲወርዱ መላእክት በእርሷ ላይ
እግዚአብሔርም ቆሞ ከላይ ከጫፏ ላይ
የአባቶችህ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ
ይህንን ምድር ለርስትህ እሰጥሃለሁኝ
ዘርህ እንደ አሸዋ በምድር ይበዛል
በአራቱም ማዕዘን ህዝብህም ይሆናል
አበው በምሳሌ እንደተናገሩት
ከምድር እስከ ሰማይ አምላክ የዘረጋት
በላይዋ ተቀምጦ በግልጽ የታየባት
የያዕቆብ ራዕይ እመቤታችን ናት
ሰማይና ምድር የሚታረቁባት
ወልደ እጓለእመህያው የተወለደባት
መላእክት በሰማይ በአንድ የዘመሩላት
ታላቋ መሰላል እመቤታችን ናት

22.ርኢክዋ ለቤተክርስትያን

ርኢክዋ ለቤተክርስትያን አፍቀርክዋ ለቤተክርስትያን(2)

ዘኢትዮጵያ(2) ቤተክርስትያን

<u>ትርጉም</u>

አየኋት ቤተክርስትያንን ወደድኳት ቤተክርስትያንን(2)

የኢትዮጵያን(2) ቤተክርስትያን

23.ቤተክርስቲያን አንተውም ከቶ

ቤተክርስቲያንን አንተውም ከቶ

የሰጠንን አምላክ በደሙ መስርቶ

የሰጠንን ጌታ በመስቀሉ ሞቶ

የአምላካችንን ቤት አንተውም ከቶ

አዝ

ሁሉንም በሁሉ በሚሞላው ጌታ

ሙሽራው የሆነች ቤቱ ተሰኝታ

በክብር በሞገስ በጸጋ ተሞልታ

ደምቃ ትኖራለች ለዓለም አብርታ(2)

አዝ

ዲያብሎስ ቢጨርስ ቀስቶቹን በሙሉ

ወጥመድ ቢዘረጋ በጉዞአችን ሁሉ

እንሻገራለን የአምላክን ስም ጠርተን

አንዳች አይነካንም እርሱን ተጠግተን(2)

አዝ

በስሙ መሰብሰብ በስሙ መስራት

ስለ ስሙ መኖር ለስሙ መሞት

ጠላት ዲያብሎስን ምን ባያስደስት

ይህ ነው ክርስትና ይኼ ነው ሕይወት(2)

አዝ

ከትውልድ ለትውልድ የምናስረክበው

ለልጅ ልጅ አውርሰን ደስ የምንሰኝው

አይደል ብርና ወርቅ አይደል ሌላ ሀብት

ሃይማኖታችን ነው የእኛ ርስት ጉልት(2)